በኣንተ ጠም

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እንዳስተማረው

፭. ጥንተ ጠም

- የሰው ልጅ በእግዚአብሔር አርአያና አምሳል ሲፈጠር መልአክ ግን ደግሞ ሥጋን የለበሰ መልአክ እንዲኾን ነው።

- ከፀሐይ ብርሃን ይልቅ ጽዱል ኾኖ እንዲኖር ኾኖ የተፈጠረ ነው።

- በትረ መንግሥቱን ይዞ፣ የንግሥና ዘውዱን ጭኖ፣ ሐምራዊ መጎናጸፍያውን አድርጎ እንዳጌጠ ንጉሥ በነጻነትና በፍጹም ደስታ ይኖር ነበር።

- አሁን የምናውቃቸው ረሀብ፣ ሕማም፣ መብለት፣ መጠማት፣ ምግብ ማማረጥ፣ መጠጥ ማማረጥ ከጥንተ ተፈጥሮዎቹ ውስጥ የሚገኙ አልነበሩም።

- እግዚአብሔር አይራብም፣ አይታመምም፣ አይበላም፣ አይጠጣምና ሰውም በአርአያውና በአምሳሉ ስለ ተፈጠረ እነዚህ ኹሉ አልነበሩበትም።

- እነዚህን ሹሉ መጠበቅ እንዲችል፣ ራሱን ገዝቶ ሌሎችንም እንዲጠብቅበት አንድ መንፈሳዊ መሣሪያ ተሰጥቶት ነበር።

- እርሱም ጦም ነው።

- ወደ ቀጣዩ ማዕርግ ማደግ ይችል ዘንድ መጠበቅ የነበረበት ነገር ጦም ነበር።

- ከዚህ ተነሥተን እንደምገነዘበው ጸጋ እንዲጠበቅ፣ በጸጋ ላይ ጸጋ እንዲጨምር፣ መንፈሳዊ ኀይል ሹሉ እንዲመነደግ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን አንድነት ኀብረት እንዲጠብቅ፣ ከፈጣሪ ጋር ሙሽራ ለመኾን የሚያገለግል ጦም አስፈላጊ ነው።

- ጦም የግድ ኀጢአት ስለ ሠሩ ብቻ የሚከናወን ሳይኾን ከላይ እንደ ተገለጠው ለአዳምና ለሔዋን የተሰጣቸው ጸጋቸውን እንዲጠብቁበት፣ ከኀጢአት እንዲጠበቁበት ነው።

- የሰው ልጅ ግን አንዲቱን ትእዛዝ - ጦም - ባለመጠበቁ ምክንያት የደረሰበትን ኹሉ ደረሰበት።፡

- በሞተ ሥጋ ላይ ሞተ ነፍስ፣ በርደተ መቃብር ላይ ርደተ ገሃነም ተፈረደበት።፡ ከእግዚአብሔርና የእግዚአብሔር ከኾኑት ተለየ።፡ የዲያብሎስ የግብር አገልጋይ ኾነ።፡ ጸጋ ራቀው።፡

- በሚያስደንቅ መልኩ በመብለቱ ኀይል ራቀው፤ ደካማ ኾነ።፡ ፍትወት ጸናበት።፡ ኀዘን፣ ትካዜ አየለበት።፡ ከጸጋ አምላክነት ወርዶ ሰው መኾንም ተሳነው።፡

- በአንዲት ትእዛዝ - ጦምን - በመተላለፉ ምክንያት ነቢያት አለቀሱ።፡

- በአንዲት ትእዛዝ - ጦምን - በመተላለፉ ምክንያት የሰው ልጅ ወደ ቀደመ ክብሩ ለመመለስ ለ5500 ዘመናት መጠበቅ ግድ ኾነበት።፡

- በአንዲት ትእዛዝ - ጦምን - በመተላለፉ ምክንያት እግዚአብሔር ሰው እንዲኾን ግድ ኾነበት።፡

፪. ጦም በብሉይ ኪዳን

- ጦም በብሉይ ኪዳን የነበሩትን ሰዎች እንደ ምን እንደ ረዳቻቸው ስንመለከት እጅግ እንደነቃለን፡፡

  - ሊቀ ነቢያት ሙሴ ሕገ አሪትንና ታቦትን የተቀበለው አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ጦሞ ነውና፡፡
  - ነቢዩ ኤልያስ እስከ ዛሬ ድረስ ሞትን ያልቀመሰው አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ጦሞ ነውና፡፡
  - ዳንኤል በአናብስት ጉድጓድ ቢጣልም አናብስቱ እንደ ለማዳ እንስሳ የኾኑለት በጦም ነውና፡፡
  - የነነዌ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቁጣ የመለሱት ዐዋቂዎቹ ሰዎች ብቻ ሳይኾኑ ጡት የሚጠቡ ሕፃናትና እንስሳትም ጭምር ጦመው ነውና፡፡
  - ከዚህ መገንዘብ እንደምችለውም ጦም ምን ያህል መንፈሳዊ ኀይል ያላት እንደ ኾነ ነው (ዘፍ.፣ ድር.1፡7)፡፡

- ከዚሁ በተቃራኒ ደግሞ፥-

  - ✓ ቀደም ብሎ እንደ ተጠቀሰው አዳም ከገነት የወጣው በስስት ድል ተነሥቶ - ባለመጠመ - ነበር።።
  - ✓ በኖኅ ዘመን የነበረው የጥፋት ውኃ የመጣው በመብል ምክንያት - ባለመጠም - ነበር።።
  - ✓ የሰዶም ሰዎች ላይ እሳትና ዲን የዘነበውም በመብል ምክንያት - ባለመጠም - ነበር (ማቴ.፣ ድር.13፡2)።።
  - ✓ ኧኤል ዘሥጋ ቢጠመም ጦማቸው ጠያፍ የነበረው እንደሚገባ ባለመጠማቸው ነበር (ኢሳ.58፡1-8)።።

፫. ጦም በሐዲስ ኪዳን

- በሐዲስ ኪዳን እንደ አዲስ ኀይልን ሰጥቶ ሥጥ (ሥልጣን ያለው) እንዲኾን ያደረገው ራሱ ጌታችን ነው።

- የሥራው ኹሉ መጀመሪያ ያደረገው ጦምን ነው።

- ጌታችን በአንድ መልኩ ጦምን በማፍረሱ የወደቀውን አዳም እርሱ ጦሞ ካሣ እንዲክሰለት፣ በሌላ መልኩ ደግሞ ለእኛ አብነት ለመኾን ጦመ።

- እንዲያውም ከተጠመቀ በኋላ መጦመ ሰዎች ከተጠመቁበት ጊዜ እንሥተው ለጦም ሊያደሉ እንደሚገባ ሲናገር ነው (ማቴ.፣ ድር.13፡1)።

- በወልድ ውሉድ፣ በክርስቶስ ክርስቲያን፣ በመንፈስ ቅዱስ መንፈሳዊ የተባለ ሰው ከተጠመቀ በኋላ መፈተኑ፡-

  - አንደኛ ከእንግዲህ ወዲህ ብርቱ መኾኑን እንዲያውቅ፣

  - ኹለተኛ [በጥምቀት] በተሰጠው መንፈሳዊ ሀብት ታላቅነት ሳይታበይ በትሕትና እንዲትጸናና ፈተናዎችም ይህን እንዲያስታውሱት፣

  - ሦስተኛ ያ ክፉው ጋኔን እንደ ከዳው ለጊዜው ስለማያምን በሚያደርስበት ፈተና ሲዋጋው ከእርሱ ጋር መኾን ፍጹም መተዉንና መራቁን ርግጠኛ እንዲኾን፣

  - አራተኛ ብረት በእሳት ሲፈተን ይበልጥ እንደሚጠነክር ክርስቲያንም በዚህ መንገድ እንዲጠነክር፣

  - አምስተኛ የተሰጡት መንፈሳዊ ሀብታት እንዳሉ በእርግጥ እንዲያውቅ ነው።

- በዚህ ኹሉ ፈተና መጽናት የሚቻለው ግን በጦም እንደ ኾነ ጌታችን ያሳይ ዘንድ ከተጠመቀ በኋላ ጦመ (ማቴ.፣ ድር.13፡1-3)።

- ቤተ ክርስቲያንም ጦም ዋነኛ መንፈሳዊ መሣሪያ እንደ ኾነ ከክርስቶስ በመማር በዐዋጅም በግልም እንድንጦም ታስተምረናለች።

- የተወደደ ጳውሎስ ምንም እንኳን የምድር መልአክ፣ የሰማይ ሰው፣ እስከ ሦስተኛው ሰማይ ድረስ የተነጠቀ፣ ዕለት ዕለት ስለ ክርስቶስ መከራ ይቀበል የነበረ ቢኾንም ይጦም ነበር። በበደል ዐዘቅት የምንኾን፣ በቅናት የተያዝነው እኛ ደግሞ ሥርየተ ኀጢአት ለማግኘት ይበልጥ ልንጦም እንዲገባን ሲያሳየን ነው (ዘፍ.፣ ድር.11፡10)።

- የቅዱስ ጳውሎስ ደቀ መዝሙር የሚኾን ቅዱስ ጢሞቴዎስ ሆዱን ያመው የነበረ ከጥብቅ ጦም የተነሣ ነበር። ፍትወታቱን ይገዛ የነበረ ጻድቅ ቢኾንም ግን ለምን እጦማለሁ ብሎ መጦሙን አለቆመም ነበር (ሐዋልታት.፣ ድር.1፡8-9)። ፍትወታት ያልራቁልን እኛ ይበልጥ እንድንጦም ያስረዳልና።

- ጦም የነፍስ ምግብ ነው። ሥጋ ምግብ በልቶ እንደሚወፍር፥ ነፍስም በጦም ትወፍራለችና። ይኸውም ንዑድ ክቡር የሚኾን ጳውሎስ በ2ኛ ቆሮ.4፡16፡- “የውጭ ሰውነታችን ሲጠፋ የውስጥ ሰውነታችን ይታደሳል” እንዳለው ነው (ዘፍ.፣ ድር.1፡9)።

- ጦም ከባድ ዐውሎ ነፋስ በበዛበት ባሕር ውስጥ እንዳለ ወደብ ነው። በዚህ ዓለም ባሕር ውስጥ ካለው ከባድና ብዙ የፈተና ዐውሎ ነፋስ የምናርፈው በዚሁ ወደብ – በጦም – ነው (ዘፍ.፣ ድር.1፡6)።

- ጦም ማለት በረጅም መንገድ ላይ እንዳሉ ማረፊያ ቦታዎች ነው። በየማረፊያ ቦታዎቹ ላይ ዐረፍ እያልን ትንፋሽ ወስደን፥ የሚበላ በልተን፥ የሚጠጣ ጠጥተን፥ ኀይል አግኝተን እንደ ገና ጉዞአችንን እንደምንቀጥል፥ እግዚአብሔርም ከቸርነቱ የተነሣ በሳምንት ኹለት ቀን እንደዚሁም ሌሎች የዐዋጅም የግል አጥዋማትን እንድንጦም በማድረግ በመንፈሳዊ ጎዳናችን ላይ ካለው ድካም ዐረፍ እንድንል፥ ይበልጥ ኀይልን ተጎናጽፈን እንድንቀጥል ያዘጋጀልን ማረፊያ ነው (ዘፍ.፣ ድር.11፡5)።

- ጦም መከር ነው። በመከር እኽል እንዲታጨድ፥ እንዲወቃና ወደ ጎተራ እንዲሰበሰብ፥ ክርስቲያንም በዚህ ወቅት በመንፈሳዊ ክረምት የደነዘ ሆዱን በጦም ስሎ መንፈሳዊ ምርት የሚያጭድበት፥ የሚወቃበትና የሚሰበሰብበት ነው (ሐዋል.፣ ድር.3፡7)።

- ጦም መድኀኒት ናት። አንድ ሕመምተኛ መድኀኒት ተገኝቶልሃል ሲባል ደስ እንዲሰኝ፥ ክርስቲያንም ጦም ሲመጣ ሐሴት ያደርጋል (ዘፍ.፣ ድር.1፡2)።

- እግዚአብሔር ስንፍናችንን፣ ቅንጦታችንን ስለሚያውቅ ከዚህ መነሻነት የሚመጣውን በደል ሥርየት እንድናገኝበት ብሎ አስቦ ጦምን መድኀኒት አደርጎ ሰጠን።

- እግዚአብሔር ከቸርነቱ የተነሣ በየጊዜው ለምንሠራው ኀጢአት ማስተስሪያ ያዘጋጀው የነፍስ ቁስል መድኀኒት ነው (ዘፍ.፣ ድር.1፡1)።

፬. የጦም አቀባበል

- ጦምን የሚቀበል ሰው ሙሽሪትን ይመስላል (ዘፍ.፣ ድር.1፡4)።

- ጦዋሚው ሙሽሪት ከኾነ ክርስቶስም ሙሽራ ነውና ጦም ግቢ ነው ማለት ነው፡፡ በጦም የሚፈጸመው የነፍስና የክርስቶስ ግቢ ነው ማለት ነው፡፡

- እንግዲህ ሙሽሪት ታገቢያለሽ ሲሉአት አዲስ የሰርግ ልብስ አሰናድታ፣ ጌጥ ሽልማት አዘጋጅታ፣ ገላዋን ታጥባ እንደምትጠበቅ፥ የክርስቲያን ነፍስም ከሙሽራ ክርስቶስ ጋር ለመዋሐድ የሰርግ ልብስ ንጽህና አሰናድታ፣ ጌጥ ሽልማት የኾኑ ምግባራትን ይዛ፣ ራስዋን በንስሐ በኑዛዜ ታጥባ ልትጠበቅ እንዲገባት ያስረዳል፡፡

፭. እንዴት መጦም ይገባል?

- ጦም መድኀኒት ናት ብለናል። መድኀኒት ደግሞ፥-
  - እንዴት እንደሚወሰድ፣
  - በየስንት ሰዓት እንደሚወሰድ፣
  - በምን ያህል መጠን እንደሚወሰድ፣
  - ለምን ዓይነት በሽታ እንደሚወሰድ፣
  - ከመድኀኒቱ ጋር የሚስማሙትንና የማይስማሙትን ምግቦች ለይቶ መረዳትን ያስፈልጋል።
  - ጦምም ልክ እንደዚህ ናት። ካልኾነ ከጥቅምዋ ይልቅ ጉዳትዋ ያመዝናልና (ሐዋልታት.፣ ድር.3፡7)።
  - እንደሚገባ ካልጦሙ በኾለት ወገን መጎዳት ነውና፥- በአንድ መልኩ በዚህ ሥጋ ይጎዳል፤ በሌላ መልኩ ደግሞ ነፍስ ምንም አክሊል አያገኝም።

- ስለዚህ ጦም በተግባር ሊገለጥ ይገባዋል፡፡ እንዴት?
  - ነዳይን በመርዳት፣
  - ከጠላት ጋር በመታረቅ፣
  - ዓይን፣ ጆሮ፣ እግር፣ እጅ፣ አንደበት፣ በአጠቃላይ ሕዋሳት ምግበ ኀጢአትን ከመብላት በመጦም (ሐውል.፣ ድር.3፡11)፣
  - በዘልማድ አለማድረግ (ዘፍ.፣ ድር.10፡2)፣
  - ከምግባራት ማለትም ከምጽዋት፣ ጥቂት ከመናገር፣ ከትሕትና፣ ከጸሎት፣ በየጊዜው ንስሐ ከመግባት ጋራ በማስተባበር (ዘፍ.፣ ድር.3፡20)፤

- ነቢዩ ዘካሪያስ በትንቢቱ ምዕ.7፡5-10 ላይ ስለ ጦም ሲናገር
  - እውነተኛ ፍርድ ከመፍረድ፣
  - ምጽዋት ከማድረግ፣
  - ችግረኛን ካለመበደል፣
  - ቂምን ከመተው ጋራ እንዲኾን ይናገራል።
- በብሉይ ኪዳን የነበረው ጦም ይህን ያህል ምግባር የተጠየቀበት ከኾነ ጽድቃችን ከጸሐፍትና ከፈሪሳውያን ሊበልጥ እንደሚገባን የተነገረንና በዘመነ ሐዲስ ያለነው እኛ ደግሞ ከዚህ በላይ እንደሚጠበቅብን ያስረዳል (ዘፍ.፣ ድር.4፡17)።

፯. የጦም ፍሬዎች

- ጦም ራሳችንን እንድንገዛ ያደርጋል (ዘፍ.፣ ድር.4፡3)።
- ራሳችንን በመግዛታችንም ተረጋግተን ቃለ እግዚአብሔርን እንድናደምጥ ያደርጋል።
- በአግባቡ ልንጦም የሚገባንም ለዚህ ነው። በአግባቡ ካልጦምን ይህን አናገኘውምና (ዘፍ.፣ ድር.2፡2)።
- ጦም የልባችን እርሻ በአግባቡ ለስልሶ የተዘራው ቃል 30፣ 60፣ 100 ያማረ ፍሬ እንዲያፈራ የሚያደርግ ማረሻ ነውና።
- በጦም ያልታረሰ እርሻ ግን በሌላ ጊዜ ለመታረስ አድካሚ ነው (ሐውል.፣ ድር.4፡2)።
- ቃለ እግዚአብሔር የሰማን እንደ ኾነም ወደ ንስሐ፣ ወደ ቤተ ክርስቲያን፣ ወደ ቁርባን፣ ወደ መንፈሳዊ ተግባራት ለመሰማራት ቀሊል ይኾንልናል።

- ጦምን እጅግ የሚንቃት ሰው ከምግበ ኀጢአት የማይከለከል ሰው ነው (ሐውል.፣ ድር.3፡11)።
- እንደሚገባ አድርጎ አለመጦም እንዲያውም አየርን እንደ መደለቅ ከንቱ ድካም ነው (ሐውል.፣ ድር.3፡7)።
- ስለዚህ በጦም ወራት ተድላ ሥጋን ከሚሰጡ ነገሮችም ጭምር መራቅ ያስፈልጋል። ለምሳሌ፡-
  - የፈረስ እሽቅድምድምን ማየት፣
  - ቲያትርን መመልከት እጅግ አሳፋሪ ሥራ ነው (ዘፍ.፣ ድር.6፡1)።
  - እነዚህን የመሰሉ ተግባራት መከወን በጦም የሚያገኙትን ሀብት በከንቱ እንደ ማባከን ነው (ዘፍ.፣ ድር.7፡1)።
  - ስለዚህ በጊዜው ታክሞ መመለስ ያስፈልጋል (ዘፍ.፣ ድር.7፡1)።

- አንድ ሰው ላይጦም ይችላል። ለምሳሌ ታምሞ (ዘፍ.፣ ድር.10፡2)።

- ይህ ሰው ታዲያ ሌሎች ምግባራትን አብዝቶ መጨመር ይኖርበታል። በሽታ ይህን እንዳያደርግ ለምሳሌ ቂም እንዳይዝ፣ ቃለ እግዚአብሔርን እንዳይማር ምክንያት አይኾንበትምና (ዘፍ.፣ ድር.10፡3)።

- እንዲያውም እንደዚህ የሚያደርግ ከኾነ አብልጦ የጦመ እርሱ ነው። የጦም ዓለማ መራብ ሳይኾን ፈቃዳተ ሥጋን መግራት ነውና (ዘፍ.፣ ድር.10፡3)።

- በጦም ውስጥ መፎካከር ያስፈልጋል። የቤተሰብ አባላት በጦም ውስጥ ምን ያህል ሠናይ ምግባራትን እንዳዳበሩ በበጎ መፎካከር ይችላሉ። በመሥሪያ ቤት ያሉ ባልንጀሮች መፎካከር ይችላሉ።

- ለምሳሌ ምን ያህል መሐላን እንደ ተዉ (ሐዉል.፣ ዳር.4፡12)።